


# አዘውትረው የሚጠየቁ የህዝብ ቆጠራ ጥያቄ እና መልስ

*በየ10 አመት፣ ዩኤስ በብሄራዊ የህዝብ ቆጠራ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ሰው ትቆጥራለች። ውጤቶቹ የገንዘብ ድጋፍ ለሚቀጠለው አሰርት አመታት እንዴት እንደሚሰራጭ ያሳውቃሉ ለትምህርት ቤቶቻችን፣ሆስፒታሎች፣ እና የህዝብ ማጓጓዣ። ቆጠራው በተጨማሪ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ምን ያክል ተወካዮች እንደሚኖሩን ይወስናል።*

**የህዝብ ቆጠራ ምንድን ነው?**
እኛ በሀገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የምንቆጥርበት መንገድ ነው—እያንዳንዱ ኗሪ፣ የስተደኛነት ሁኔታው ምንም ቢሆን።

**የዜግነት ጥያቄ አለው?**
የለም —የህዝብ ቆጠራው ስለ ዜግነት ወይም የስደተኛነት ሁኔታ ምንም ጥያቄ የለውም።

**ህዝቡን መቁጠር ለመንግስት አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?**
መንግስት ገንዘብ የሚፈለግበት ቦታ የት እንደሆነ የሚያውቅበት መንገድ ነው — እንደ ሆስፒታሎች፣ትምህርት ቤቶች፣ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት፣ እና ማጓጓዣ። በተጨማሪ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ዋሺንግተን ምን ያክል ተወካዮች እንደሚኖራት ይወስናል።

**እኔ በህዝብ ቆጠራው ለምን እሳተፋለሁ?**
እርስዎ የህዝብ ቆጠራውን ሲሞሉ፣ ሊደረግልን ስለሚገባ የገንዘብ ድጋፍ እና ስለውክልናችን የሚወስነው ዳታ ላይ የኛ ማህበረሰብ በሙሉ መወከሉን ያረጋግጣሉ። የእርስዎ ተሳትፎ የታክስ ዶላሮችዎ ወደ ማህበረሰብዎ ተመልሰው እንዲመጡ ይረዳል።

**የህዝብ ቆጠራው መቼ ነው የሚደረገው?**
ከማርች 12 ጀምሮ፣ ሰዎች የህዝብ ቆጠራውን እንዴት መሙላት እንዳለባቸው መረጃ በፖስታ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል። እርስዎ እስከ ጁላይ 31 ኦንላይን መሙላት ይችላሉ። እርስዎ ኢንተርኔት የማያገኙ ከሆነ ወይም ደግሞ እርዳታ ካስፈለግዎ፣ በማህበረሰብዎ ውስጥ የህዝብ ቆጠራውን በእርዳታ መሙላት የሚቻልባቸው ቦታዎች አሉ።

**ማን መቆጠር አለበት?**
ከኤፕሪል 1፣2020 ጀምሮ ቤተሰብዎ ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው በህዝብ ቆጠራው ቅጽ መቆጠር አለባቸው። ይህ የሚያካትተው ልጆችን እና ከኤፕሪል 1 ጀምሮ የተወለዱ ህጻናቶች እስከ አዛውንቶች፣ ዘመዶች እና ዘመዶች ያልሆኑ፣የስደተኛነት ሁኔታቸው ምንም ቢሆን። ቤተሰብዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ከአንድ በላይ በሆነ ቤት ውስጥ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ ከሆነ፣ እነሱ አብዛኛውን ጊዜ በሚኖሩበት እና በሚተኙበት ቦታ መቆጠር አለባቸው።

**የህዝብ ቆጠራውን እንዴት እሞላለሁ?**
የህዝብ ቆጠራውን በቀላሉ መሙላት የሚቻልበት መንገድ ኦንላይን ነው በ **2020census.gov**። በተጨማሪ እርስዎ በስልክ ወይም በወረቀት ቅጽ መሙላት ይችላሉ።

**ለበለጠ መረጃ የት እሄዳለሁ?**
ይጎብኙ **2020census.gov** ወይም በዚህ ወረቀት ጀርባ ላይ በተዘረዘረው የህዝብ ቆጠራ ቢሮ ላይ ከክፍያ ነጻ ይደውሉ።



የህዝብ ቆጠራ
2020
2020census.gov

# እኛ እዚህ ነን። እኛ እናስፈልጋለን።

## ከማርች 1 በኋላ፣ ለእርዳታ ይደውሉ በ፣

| የቋንቋ መስመር | | ከክፍያ ነጻ ቁጥር |
|---|---|---|
| English | | 844-330-2020 |
| Spanish | Español | 844-468-2020 |
| Chinese (Mandarin) | 普通话 | 844-391-2020 |
| Chinese (Cantonese) | 广东话 | 844-398-2020 |
| Vietnamese | Tiếng Việt | 844-461-2020 |
| Korean | 한국어 | 844-392-2020 |
| Russian | Русский | 844-417-2020 |
| Arabic | العربية | 844-416-2020 |
| Tagalog | Wikang Tagalog | 844-478-2020 |
| Polish | Język Polski | 844-479-2020 |
| French | Français | 844-494-2020 |
| Haitian Creole | Kreyòl Ayisyen | 844-477-2020 |
| Portuguese | Português | 844-474-2020 |
| Japanese | 日本語 | 844-460-2020 |
| English (Puerto Rico) | | 844-418-2020 |
| Spanish (Puerto Rico) | Español (Puerto Rico) | 844-426-2020 |
| Telephone Display Device (TDD) | | 844-467-2020 |